# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ

## የገበያ ልማትና ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 74/2014

## መግቢያ

መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቅረጽ ለስራ አጥ ዜጎች የስራ ዕድልን በመፍጠርና በከተማችን የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡በዚህ መሰረት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት የተደራጁ ዜጎችን የገበያ ድጋፍ በመስጠት በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተደራጅተው የሚሰሩ ኢንተርፕራይዞች የውጭ ምርት እንዲተኩና በገበያው ላይ የሚታየውን የአቅርቦት ችግር በመቅረፍ ለከተማዋ ነዋሪ ህብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ እገዛ እየተደረገ ነው፡፡

በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ተደራጅተው ወደ ሥራ ለሚገቡ ነዋሪዎች በአካባቢ፣ በክልልና በውጭ ገበያ ተጠቃሚ የሚሆንበትን የድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ የሚገኝ ቢሆንም እስካሁን ያለው የገበያ ድጋፍ አሰጣጥ ሁኔታ የኢንተርፕራይዞችን ብቃትና ተወዳዳሪነት የማያበረታታና ውስን ኢንተርፕራይዞችን ብቻ የሚያሳትፍ እንደነበር ይታወቃል፡፡

የገበያ ልማትና ግብይት አገልግሎቶች ኢንተርፕራይዞች ከሚፈልጉት ድጋፍ አንፃር ፍትሃዊነት የጎደለው፣ግልጽነትና ተጠያቂነት የሌለው፤ የኢንተርፕራይዞችንና ምልልስ የሚጨምር ለብልሹ የሆኑ አሰራሮች ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ከመፍጠር አንፃር ክፍተት የነበረበት መሆኑን ለማየት የተቻለ ሲሆን ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና ወጥነት ያለው የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3)(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. . አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የገበያ ልማትና የግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 74/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፥

1. **"ቢሮ"** ማለት የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ነው፡፡
2. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በክፍለ ከተማና በወረዳ የሚገኙ የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽህፈት ቤት ነው፡፡
3. **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ ቤተሰብና በስሩ የቀጠራቸውን ሠራተኞች ጨምሮ እስከ 5 ሰው ቀጥሮ የሚያሰራና ለኢንዱስትሪ ከሆነ የጠቅላላ ሃብት እስከ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺ/ ወይም ለአገልግሎት ዘርፍ ጠቅላላ ሃብቱ እስከ 50,000.00 /ሃምሳ ሺ /የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡
4. **"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ ቤተሰብና በስሩ የቀጠራቸውን ሠራተኞች ጨምሮ ከ6-30 ሰው ቀጥሮ የሚያሰራና ለኢንዱስትሪ ከሆነ የጠቅላላ ሃብት ከብር 100,001.00 /አንድ መቶ ሺ/ እስከ ብር 1,500,000.00 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ/ ወይም ለአገልግሎት ዘርፍ ጠቅላላ ሃብቱ ከብር 50,001.00 /ሃምሳ ሺ አንድ/ እስከ ብር 500,000.00 /አምስት መቶ ሺ/ የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡
5. **"ገበያ"** ማለት በአካባቢ፣ በክልልና በውጪ ሀገር ደረጃ የሚገኝና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት በዋጋ ተወዳዳሪ ሆነው የሚቀርቡበት ስፍራ ነው፡፡
6. **"ግብይት"** ማለት በሻጭ እና በገዥ መካካል የሚካሄድ የምርትና አገልግሎት ልውውጥ ማለት ነው፡፡
7. **"የገበያ ትስስር"** ማለት በአካባቢ ፣ በክልልና ሀገር አቀፍ እንዲሁም በውጪ ሀገር በሚፈጠሩ የገበያ ዕድሎች በነጻ ገበያ መርህ ላይ በተመሰረተ የገበያ ውድድር የእርስ በርስ ወይም በተዋረድ ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በንዑስ ተቋራጭነት ፣በአውትሶርሲንግ፣ በፍራንቻይዚንግ በአውትግሮወር እና በሌሎችም የግብይት ዘዴዎች ተሳስረው ምርትና አገልግለት በማቅረብና በመቀበል የሚደረግ የገበያ ልውውጥ ነው፡፡
8. **"የአካባቢ ገበያ"** ማለት በአዲስ አበባ ክልል ውስጥ ሆኖ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ ክልል ውስጥ የሚፈጠር ገበያ ነው፡፡
9. **"የክልል ገበያ ትስስር"** ማለት ከአዲስ አበባ ክልል ውጪ በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል ከሚገኝ ማንኛውም የመንግስት ድርጅት፣ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የመካከለኛና

ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ወይም የህብረት ሥራ ዩኒዮን በከተማችን ካሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር በገበያ ማስተሳሰር ነው፡፡

10. **"የውጪ ገበያ"** ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄድ የንግድ ወይም የግብይት ሥርዓት ሆኖ በሀገር ውስጥ የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በውጭ ሀገር ከሚገኙ ተቋማት ጋር ምርትና አገልግሎታቸውን በተለያዩ የግብይት መንገዶች የሚለዋወጡበት ሥርዓት ነው፡፡
11. **"እሴት መጨመር"** ማለት አንድ ምርት ወይም አገልግሎት በፊት ከነበረበት አካላዊ ወይም ውስጣዊ ይዘት ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ተጨማሪ ገጽታ መፍጠር ነው፡፡
12. **"ንዑስ ስራ ተቋራጭነት"** ማለት የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወይም የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመለየት ሥራውን በከፊል በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሰራ ውል በመፈጸም የሚካሄድ የግብይት ሥርዓት ነው፡፡
13. **"አውትሶርሲንግ"** ማለት በመንግስታዊ፤መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እና ኩባንያዎች የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በጥቃቅንና አነስተኛ የሚቀርብበት የግብይት ሥርዓት ነው፡፡
14. **"ፍራንቻይዚንግ"** ማለት በተወሰኑ ለየት ባሉ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ከአምራቹ ወይም አገልግሎት ሰጪው ወይም አከፋፋዩ ድርጅት ጋር የንግድ ስምምነት ውል በመፈጸም በውሉ መሰረት በውል ሰጪው የንግድ ስም፤ምልክትና ፈቃድ የሚፈጸም የንግድ አሰራር ሥርዓት ነው፡፡
15. **"አውትግሮወር"** ማለት በአግሮፕሮሰሲንግ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጓቸውን የግብርና ግብዓቶች በኢንተርፕራይዞች ተመርቶ ወይም እሴት ተጨምሮበት ከኢንዱስትሪዎች ጋር በሚደረግ ስምምነት ውል በመፈጸም የሚቀርብበት የንግድ አሰራር ሥርዓት ነው፡፡
16. **"የገበያ ዳይሬክተሪ"** ማለት የአንተርፕራይዞችን እና አምራቾች አድራሻ መረጃ የምናስተዋውቅበት የማስተዋወቂያ ዘዴ ነው፡፡
17. **"ኢ-ኮሜርስ"** ማለት ኢንተርፕራይዞች በተለያዩ ድረ ገጾችን በመክፈት ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት የግብይት መሳሪያ ነው፡፡
18. **"ካታሎግ"** ማለት ኢንርተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎታቸውን በዝርዝር በህትመት በፎግራፍ በማስደገፍ ምርትና የምርት ናሙናቸውን የሚያስተዋውቁበት የማስታዋወቂያ መሳሪያ ነው፡፡
19. **"ቴሌማርኬቲንግ"** ማለት በስልክ ደንበኞችን በመለየት የምርት ናሙና የምናስተዋውቅበት እና ሽያጭ የሚካሄድበት የግብይት መንገድ ነው፡፡
20. **"ሞዴል ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፕሮግራም ታቅፎ በራስ ጥረትና የተደረገለትን መንግስታዊ ድጋፍ በመጠቀም ለላቀ ውጤት የበቃና በልማታዊ አመለካከቱ ለሌሎች መሰል ኢንተርፕራይዞች አርያ

በመሆን በማስፋት ስትራቴጂ ላይ ግንባር ቀደም የልማት ሃይል የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፡፡

21. **"የኢንተርፕራይዝ ደረጃ ሽግግር"** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ በዕድገት ደረጃው የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃ የሽግግር መስፈርቶቹን በማሟላት መሻገር ሲችል ነው::
22. **"የምሥረታ ወይም ጀማሪ ደረጃ"** ማለት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ለመመሥረት ፍላጎት ያላቸው ነዋሪዎች በግል፣ በህብረት ሽርክና ማህበር፣ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አክሲዮን ማህበር ተደራጅተው ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ማምረትና አገልግሎት መስጠት ተግባር የሚጀምሩበት ነው::
23. **"የታዳጊ ወይም መስፋፋት ደረጃ"** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሲሆንና ትርፋማነቱ ቀጣይነት ሲኖረው ነው:: በዚህ ደረጃ ያለ ኢንተርፕራይዝ በምሥረታ ደረጃ ከነበረው ቀጥሮ የሚያሠራው የሰው ኃይል ቁጥርና የጠቅላላ ሃብት መጠን ዕድገት በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የሚጠቀም ነው::
24. **"የመብቃት ደረጃ"** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የገበያ ድርሻውን ለማሳደግ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በሥራ ላይ ካዋለና ለዘርፉ የተቀመጠውን ትርጓሜ መስፈርት ሲያሟላና ወደ ታዳጊ መካከለኛ ሲሸጋገር ወይም በአለበት ደረጃ ጥቃቅን ወይም አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በመሆን በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን ነው::
25. **"ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ"** ማለት ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተቀመጠውን የሰው ሃይልና ጠቅላላ ሃብት መጠን የመብቃት የዕድገት ደረጃ በማለፍ ወደ ኩባንያ ደረጃ የተሸጋገረ የኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ማለት ነው::
26. **"ክላስተር"** ማለት በአንድ አካባቢ ተሰብስበው ብዛት ያላቸውና ተመጋጋቢ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን የሚያቀርብና ተመሳሳይ ሃላፊነትንና መልካም አጋጣሚውንም የሚጋሩ ተቋማት ስብስብ ነው፥
27. **"የተጣራ ካፒታል" ማለት** አንድ ኢንተርፕራይዝ ጠቅላላ የሃብት መጠን ሲቀነስ እዳ ማለት ነው፡፡
28. **"የምርት ወይም የአገልግሎት ማስታወቂያዎች"** ማለት ምርትን ወይም አገልግሎትን ለማስተዋወቅ የመገናኛ ብዙሃን፣ ንግድ ትርዒትና ባዛር፣ ብሮሸር፣ በራሪ ወረቀት፣ ዳይሬክተሪ ፣ካታሎግ፣ ድረ ገጽ፣ ቢዝነስ ካርድ፣ ቋሚ የማስታወቂያ ሰሌዳና ማሸጊያን ያካተተ ነው፡፡

29. **"የታከለ ዋጋ"** ማለት ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጪ ሀገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጪ አገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ነው፡፡

30. **"ጥሬ ዕቃ"** ማለት አንድን ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የምንጠቀምበት ግብዓት ነው፡፡

31. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

32. በዚህ መመሪያ ውስጥ **በወንድ** ፆታ የተገለፀው **የሴትንም** ፆታ ያካትታል፡፡

### 3. . የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮና በስሩ ባሉት ተቋማት እና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ዓላማ፤ አስፈላጊነት እና መርሆች

### 4. የመመሪያው ዓላማ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቱትን ምርትና የሚሰጡትን አገልግሎት በጥራት፣ በተወዳዳሪ ዋጋና በብዛት በማቅረብ የአካባቢ፣ የክልልና የአገር አቀፍ የገበያ ዕድሎችን በመጠቀም ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

### 5. . የመመሪያው አስፈላጊነት

1. የኢንተርፕራይዞችን ዕድገት ደረጃ ታሳቢ ያደረገና ወጥነት ያለው አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፡፡
2. የገበያ ትስስር ድጋፍ ብልሹ ከሆኑ አሰራር የጸዳ፣ አሳታፊ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማቅረብ፣
3. ኢንተርፕራይዞች ከጠባቂነት በመላቀቅ በነፃ ውድድር በጥራትና በዋጋ በገበያው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ በማስፈለጉ፤

## 6. የመመሪያው መርሆዎች

1. የሚሰጡ የገበያ ድጋፎች የጠባቂነትና አመለካከት የሚቀርፉ ኢንተርፕራይዞቹ ችግራቸውን በመለየትና መፍትሔ በማፈላለግ ሂደት ውስጥ ግንባር ቀደም የሚሆኑበት፣
2. የሚሰጡ የገበያ ድጋፎች በግልጽ መስፈርት ላይ የተመሠረቱ፣ የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ መሰረት ያደረጉ፣ የተቀናጁና ተወዳዳሪነትን የሚያጎለብቱ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3. የገበያ ዕድሎችን አሟጦ መጠቀም፤
4. በጥራትና በዋጋ ላይ የተመሰረተ የገበያ ተወዳዳሪነትን መከተል፣
5. የንግድ አሰራርን መሠረት ያደረገና ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የግብይት ሥርዓት መፍጠር፣
6. ለሴቶች፣ ለወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ለስደት ተመላሾች እንዲሁም ለዩኒቨርሲቲና ኮሌጅ ምሩቃን ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ትኩረት መስጠት፡፡

# ክፍል ሶስት
# የገበያ ትስስር ዓይነቶች እና የግብይት ሥርዓቶች

## 7. የገበያ ትስስር ዓይነቶች

1. በአካባቢ የሚፈጠር የገበያ ትስስር፣
2. በክልል የሚፈጠር የገበያ ትስስር፣
3. በውጪ ሀገር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፡፡

## 8. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአካባቢ የሚፈጠር የገበያ ትስስር ዓይነቶች

1. መንግስታዊ ከሆኑ ተቋማት ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
2. መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
3. ከፍተኛና መካከለኛ ኢንድስትሪዎች ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
4. በኢንተርፕራይዞች መከካል እርስ በርስ የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
5. የግል ሸማቾች እና ከሸማቾች መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበራት እንዲሁም ከዩኒየኖች ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
6. ከአካባቢ ማህበረሰብ ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
7. ከግለሰቦች ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤

8. የፋይናስ ተቋማት፤ ከግል ንግድ ድርጅት ተቋማት ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤

9. ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በተቋማት ወይም ወኪሎች መካከል የሚካሄድ ትስስር፤

10. በቴሌ ማርኬቲንግ የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤

11.በኤሌክትሮኒክስ ግብይት የሚፈጠር የገበያ ትስስር፡፡

## 9. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የአካባቢ ገበያዎችን አሟጦ ስለመጠቀም

1. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መንግስታዊ ከሆኑ ተቋማት የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤የፋይናስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ባወጣው የግዢ መመሪያ መሰረት አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፣ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈፃሚ መደረግ አለበት፡፡ ይኸውም፡-

   ሀ. ለመድህኒት እና የህክምና መሳሪያዎች ግዢ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ ቅናሽ የሚያገኙ መሆን አለበት፤

   ለ. ለሌሎች ዕቃዎች ግዢ 15% /አስራ አምስት በመቶ/ ቅናሽ የሚያገኙ መሆን አለበት፤

   ሐ. ለግንባታ ሥራና የምክር አገልግሎት ግዥዎች 7.5% /ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ/ ቅናሽ የሚያገኙ መሆን አለበት፡፡

2. የሚደረገው ልዩ አስተያየት መድሐኒቱን ወይም የህክምና መሳሪያውን ወይም ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ዋጋ ወጪ 35% /ሰላሳ አምስት በመቶ/ እና ከዚያ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ ቅናሽ መደረግ አለበት፡፡

3. ማንኛውም የግንባታ ዘርፍ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲያሟላ መሆን አለበት ፡፡

   ሀ. ማህበሩ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመና እና ዋና መስሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

   ለ. ማህበሩ አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ50% /ሃምሳ በመቶ/ በላይ በኢትዮጵያውያን የተገዛ ከሆነ፣

   ሐ. ከማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ50% /ሃምሳ በመቶ/ በላይ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

መ. ማህበሩ ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ ከ50% /ሃምሳ በመቶ/ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፡፡

4. በስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ የተቋቋሙ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፡-

ሀ. ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሚያደርጉት ውድድር 3% /ሦስት ከመቶ/ ልዩ አስተያየት መደረግ አለበት፡፡

ለ. ግዢው በአለም አቀፍ የግዥ ዘዴ የሚፈፀም ሲሆን የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈፃሚ መደረግ አለበት፡፡

ሐ. በጨረታ ማስከበሪያ ፣ በውል ማስከበሪያ እና የቅድመ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱ ያደራጃቸው አካል የሚሰጥ የዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፡፡

መ. ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሠነድ በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋምነት የተቋቋሙበትን የህጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለ ክፍያ በነፃ መሰጠት አለበት፡፡

## 10. በመንግስት ተቋማት በሚፈጠሩ የገበያ ድጋፎች ኢንተርፕራይዝ ምልመላን በተመለከተ፡-

1. የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ማከናወን አለበት፡፡
2. ገበያውን የፈጠረው ተቋም የሚያወጣቸው መስፈርቶች ከኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ጋር የማይገናዘቡ ሆኖ ሲገኝ ገበያውን ከሚፈጥረው ተቋም ጋር በመወያየት በሚዘጋጁ መስፈርቶች መሰረት የሚፈጸም መሆን አለበት፡፡
3. የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም መስፈርት ሳያዘጋጅ ስራውን በጥቃቅንና አነስተኛ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች መስጠት የፈለገ ከሆነ ያደራጃቸው አካል ስራው ከሚጠይቀው የሰው ኃይልና ካፒታል አንፃር መስፈርት በማዘጋጀት የሚፈጸም መሆን አለበት፡፡
4. ኢንተርፕራይዙን ያደራጀው አካል የመመልመያ መስፈርቱን ግልጽ በማድረግ በውድድር ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም መሆን አለበት፡፡
5. የመመልመያ መስፈርቱ ለኢንተርፕራይዞች ግልጽ ሆኖ የሚቀይበት ጊዜ የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም በሚያዘጋጀው መስፈርትና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚፈፀም መሆን አለበት፡፡

## 11. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በዕድገት ደረጃ መሰረት በኮንስትራክሽን ዘርፍ በአልሙኒየም በርና መስኮት መግጠም ስራዎች ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች እስከ ብር 5,000,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

1. ለጥቃቅን ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 340,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

2. ለጥቃቅን ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ ከብር 340,001.00 እስከ ብር 950,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

3. ለጥቃቅን መብቃት ኢንተርፕራይዝ ከብር 950,001.00 እስከ ብር 1.500,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

4. ለአነስተኛ ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 1.500,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

5. ለአነስተኛ ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ ከብር 1.500,001.00 እስከ ብር 3,000,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

6. ለአነስተኛ መብቃት ኢንተርፕራይዝ ከብር 3,000,001.00 እስከ ብር 5,000,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

**12. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በዕድገት ደረጃ መሰረት በአገልግሎት፣ በንግድ እና በከተማ ግብርና ስራዎች ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች እስከ ብር 1,500,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡**

1. ለጥቃቅን ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 170,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

2. ለጥቃቅን ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ ከብር 170,001.00 እስከ ብር 350,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

3. ለጥቃቅን መብቃት ኢንተርፕራይዝ ከብር 350,001.00 እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

4. ለአነስተኛ ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

5. ለአነስተኛ ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ ከብር 500,001.00 እስከ ብር 900,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

6. ለአነስተኛ መብቃት ኢንተርፕራይዝ ከብር 900,001.00 እስከ ብር 1,500,000.00ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

**13. በጥቃቅን ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃን መሰረት በማድረግ እስከ ብር 3,000,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር ስለመፍጠር**

1. ለጥቃቅን ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 500,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

2. ለጥቃቅን ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ ከብር 500,001.00 እስከ ብር 900,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

3. ለጥቃቅን መብቃት ኢንተርፕራይዝ ከብር 900,001.00 እስከ ብር 1,200,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

4. ለአነስተኛ ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ እስከ ብር 1,200,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

5. ለአነስተኛ ታዳጊ ኢንተርፕራይዝ ከብር 1,200,001.00 እስከ ብር 2,000,000.00 ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

6. ለአነስተኛ መብቃት ኢንተርፕራይዝ ከብር 2,000,001.00 እስከ ብር **3,000,000.00** ድረስ የገበያ ትስስር መፈጠር አለበት፡፡

**14. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 እስከ አንቀጽ 14 ድረስ የተገለጽው የብር መጠን ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-**

1. አንድ ገበያ ትስስር ከአንድ በላይ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች እንደ ገበያው የብር መጠን በመስጠት የሚተገበር መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ በኮንስትራክሽን ዘርፍ፣ በአልሙኒየም በርና መስኮት መግጠም ስራዎች ከጀማሪ እስከ ታዳጊ መካከለኛ እስከሚደርስ ድረስ የሚፈጠርለት የገበያ ትስስሮች ተደምረው ከብር 5,000,000.00 መብለጥ የለበትም፡፡
3. ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ በአገልግሎት፣ በንግድ እና በከተማ ግብርና ስራዎች ከጀማሪ እስከ ታዳጊ መካከለኛ እስከሚደርስ ደረስ የሚፈጠርለት የገበያ ትስስሮች ተደምረው ከብር 1,500,000.00 መብለጥ የለበትም፡፡
4. ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ስራዎች ከጀማሪ ጥቃቅን እስከ ጥቃቅን መብቃት እስከሚደርስ ድረስ የሚፈጠርለት የገበያ ትስስር ተደምሮ ከብር 3,000,000.00 መብለጥ የለበትም፡፡
5. አንድ ኢንተርፕራይዝ ምን ያህል መጠን ያለው ስራ እንደሰራ ክትትል በማድረግ በተቀመጠው ጣሪያ ላይ ሲደርስ ውል የማቋረጥ ወይም ከውድድር ውጪ የማድረግ ኃላፊነት የአሰሪው መስሪያ ቤት መሆን አለበት፡፡
6. የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ አንድ ኢንተርፕራይዝ ምን ያህል መጠን ያለው ስራ እንደሰራ ክትትል በማድረግ በተቀመጠው ጣሪያ ላይ ሲደርስ አሰሪው መስሪያ ቤት ውል ያቋረጠ ስለመሆኑ ክትትል የማድረግ ስራ መስራት አለበት፡፡

7. የአሰሪው መስሪያ ቤት የፈጠረውን የገበያ ትስስር ወቅታዊ መረጃ በመሰብሰብ መያዝ አለበት፡፡
8. በመንግስት ፕሮጀክት ሆነ በመንግስት ግዢ ዕድል ያገኙ ኢንተርፕራይዞች ተገቢውን የዕድገት ደረጃ እየተሰጣቸው የገበያ ትስስር ጣሪያ ሲደርሱ በዕድገት ደረጃ ባለሙያ ክትትል እየተደረገ ወደ ቀጣዩ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ መደረግ አለበት፡፡
9. ታዳጊ መካካለኛ የዕድገት ደረጃ የደረሰ ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ከመንግስት የድጋፍ ማዕቀፍ ውጪ መሆን አለበት፡፡
10. የገበያ ትስስር ድጋፍ ሲደረግ የኢንተርፕራይዙን አባላት ቁጥር ታሳቢ በማድረግ ቅድሚያ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡
11. አንድ ጊዜ የገበያ ትስስር ያገኘ ኢንተርፕራይዝ ለሁለተኛ ጊዜ ትስስር የሚደረግለት በዘርፉ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሌሎች ኢንተርፕራይዞች የመጀመሪያ ትስስር ማግኘታቸውን በማረጋገጥ መሆን አለበት፡፡
12. የገበያ ትስስር የሚደረግለት ኢንተርፕራይዝ የበጀት ዓመቱን የዕድገት ደረጃ ያሳደሰ መሆን አለበት፡፡

## 15. የግብይት ሥርዓት ዓይነቶች፡-

የገበያ ትስስር የሚፈጠርባቸው የግብይት ሥርዓት ዓይነቶች፡-

1. ንዑስ ስራ ተቋራጭነት፣
2. የአውትሶርሲንግ፣
3. ፍራንቻይዚንግ፣
4. አውትግሮወር፡፡

## 16. ከገበያ ትስስር ድጋፍ ውጪ ስለማድረግ

1. ኢንተርፕራይዙ ወደ ታዳጊ መካከለኛ ሲሸጋገር፣

1. የተሰጠውን ስራ በገባው ውል መሰረት መፈጸም ሳይችል ሲቀር፣
2. የተጭበረበረ መረጃ አቅርቦ ሲገኝ የገበያ ትስስር ይቋረጣል፡፡

# ክፍል አራት
# የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቅ

## 17. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት የማስተዋወቂያ ስልቶች

1. በኤግዚቪሽንና ባዛር፣
2. በድረ - ገጽ፣
3. በዳይሬክተሪ፣
4. በካታሎግ፣
5. በመጽሔት፣

3. በብሮሸር፣
4. በበራሪ ወረቀት፣
5. በቴሌቪዥንና ሬዲዮ፣
6. በታዋቂ ሰዎች፣
7. ቤት ለቤት የሚደርግ፣
8. በህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች፡፡

## 18. በኢግዚቢሽንና ባዛር ምርትና አገልግሎት ስለማስተዋወቅ

**1. የኢግዚቪሽንና ባዛር አዘገጃጀትን በተመለከተ፡-**

ሀ. በአዲስ አበባ ከተማ ክልል የሚዘጋጅ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኢግዚቪሽንና ባዛር ደረጃውን የጠበቀ መሆን አለበት፡፡

ለ. የኢግዚቪሽን እና ባዛሩን ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያግዙ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለባለሙያዎችና ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የግንዛቤ ፈጠራ ስልጠናዎች መዘጋጀት አለበት፡፡

ሐ. ኢግዚቪሽንና ባዛር የሚዘጋጅበት ቦታ ብዙ ህዝብ የሚንቀሳቀስበት ቦታ እና ሰፊ ገበያ ዕድል የሚፈጥር መሆን አለበት፡፡

መ. ኢግዚቪሽንና ባዛር ሲዘጋጅ የትራፊክ ፍሰትን የማያስተጓጉል እና ለአደጋ ያልተጋለጠ መሆን አለበት፡፡

**2. በኢግዚቪሽንና ባዛር የሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞች ምልመላን በተመለከተ**

ሀ. በበጀት ዓመቱ የታደሰ የዕድገት ደረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

ለ. ዕድገት ተኮር የስራ ዘርፍ ላይ የተሰማራ መሆን አለበት፡፡

ሐ. ከንግድ ዘርፍ ውጪ ያለ ኢንተርፕራይዝ የራሱን ምርት ብቻ ይዞ መግባት አለበት፡፡

3. በኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ የሚሳተፉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ

ሀ. አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም፣

ለ. የፈጠራ ስራ ያለው፣

ሐ. የውጪ ምርት የሚተካ፣

መ. ሞዴል ኢንተርፕራይዝ የሆነ፣

ሠ. ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠረ፣

ረ. ምርታቸውን ወደ ውጪ ሀገር ለሚልኩ ቅድሚያ የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

ሰ. አካል ጉዳተኝነትን እና ኤች አይ ቪ ቫይረስ ተጋላጭ የሆኑ ህብረተሰብ ክፍሎች መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

ሸ.ሴቶችና ወጣቶችን፣ ከስደት ተመላሾችን፣ የዩኒቨርሲቲና የቴክኒክን ሙያ ምሩቃን አንቀሳቃሾችን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

4. የኤግዚቢሽንና ባዛር ተሳትፎን በተመለከተ

ሀ. በኤግዚቢሽንና ባዛር የሚሳተፉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አምራች 60%፣ ከተማ ግብርናና አገልግሎት ሰጪ 25% መሆን አለበት፡፡

ለ. በንግድ ዘርፍ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ተሳታፊ የሚሆኑት 15% መሆን አለበት፡፡

ሐ. ኢንተርፕራይዞች ከኤግዚቢሽንና ባዛር አዘጋጅ አካል በተሰጣቸው ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቂያ ቦታ የኢንተርፕራይዙን ማንነት የሚገልፅ ቢዝነስ ካርድ፣ ባነር ማዘጋጀትና ማስዋብ አለባቸው፡፡

መ. በኤግዚቢሽንና ባዛር የተሳተፉ ኢንተርፕራይዞች አዘጋጁ አካል ኢግዚቢሽንና ባዛሩን በተመለከተ የሚጠይቃቸውን አጠቃላይ መረጃዎች መስጠት አለባቸው፡፡

5. **የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከክፍለ ከተማቸው ወይም ከወረዳቸው ውጪ ተሳትፎን በተመለከተ፡-**

ሀ. አዘጋጁ አካል ያደራጃቸውን ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ በመስጠት ተጨማሪ ቦታ ካለው ብቻ ከሌላ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ማሳተፍ አለበት፡፡

ለ. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከክፍለ ከተማ ወደ ክፍለ ከተማ ወይም ከወረዳ ወደ ወረዳ ሄደው የሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞች በራሳቸው ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ኢግዚቢሽንና ባዛር ያልተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

6. **በከተማ ደረጃ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኢግዚቢሽንና ባዛር ስለማዘጋጀት**

ሀ. በከተማ ደረጃ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የደረሱበትን ደረጃ እና ውጤታማነት የሚያሳይ ኤግዚቢሽንና ባዛር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መዘጋጀት አለበት፡፡

ለ. ከተለያዩ ክልሎች የሚመጡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቢሮ በሚያዘጋጀው ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ ባለው ክፍት ቦታ ሊያሳትፋቸው ይችላል፡፡

ሐ. በከተማ ደረጃ የሚዘጋጅ ኤግዚቢሽን እና ባዛር በማምረት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ በዋናነት ሞዴል እና በመብቃት የዕድገት ደረጃ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞችን ቅድሚያ በመስጠት ሌሎችም እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፡፡

መ. በሚዘጋጅ ኢግዚቢሽንና ባዛር ሁሉም ኢንተርፕራይዞች ያለምንም ክፍያ በነጻ መሆን አለባቸው፡፡

ሠ. ኢግዚቪሽንና ባዛር በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የሚዘጋጅ ሆኖ የአንድ ዙር ዝግጅት የቆይታ ጊዜ ከሰባት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

**7.በክፍለ ከተማ ደረጃ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኢግዚቪሽንና ባዛር ስለማዘጋጀት፣**

ሀ. በክፍለ ከተማ ደረጃ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የደረሱበትን ደረጃ እና ውጤታማነት የሚያሳይ ኤግዚቢሽንና ባዛር መዘጋጀት አለበት፡፡

ለ. በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚዘጋጅ ኢግዚቪሽን እና ባዛር በዋናነት በሞዴል እና ታዳጊ የዕድገት ደረጃ የሚገኙ በማምረት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞችን ቅድሚያ በመስጠት ሌሎቹንም እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፡፡

ሐ. በሚዘጋጅ ኢግዚቪሽንና ባዛር ሁሉም ኢንተርፕራይዞች ያለምንም ክፍያ በነጻ መስተናገድ አለባቸው፡፡

መ. ኢግዚቪሽንና ባዛር ቢያንስ በዓመት 4 ጊዜ የሚዘጋጅ ሆኖ የአንድ ዙር ዝግጅት የቆይታ ጊዜ ከ 7 ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

**8. በወረዳ ደረጃ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኢግዚቪሽንና ባዛር ስለማዘጋጀት፣**

ሀ. በወረዳ ደረጃ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የደረሱበትን ደረጃ እና ውጤታማነት የሚያሳይ ኢግዚቪሽንና ባዛር መዘጋጀት አለበት፡፡

ለ. በወረዳ ደረጃ የሚዘጋጅ ኢግዚቪሽን እና ባዛር በዋናነት በማምረት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የዕድገት ደረጃቸው ጀማሪ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ በመስጠት ሌሎቹንም ያሳተፈ መሆን አለበት፡፡

ሐ. በሚዘጋጅ ኢግዚቪሽንና ባዛር ሁሉም ኢንተርፕራይዞች ያለምንም ክፍያ በነጻ መሰራት አለበት፡፡

መ. ኢግዚቪሽንና ባዛር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚዘጋጅ ሆኖ የአንድ ዙር ዝግጅት የቆይታ ጊዜ ከሰባት ቀን መብለጥ የለበትም፡፡

ሠ. አንድ ወረዳ ለብቻው ኢግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀት የማይቻል ከሆነ ከሌሎች ወረዳዎች ጋር በመቀናጀት ኢግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀት ይችላል፡፡

**9. በክልሎች ስለሚካሄድ ኢግዚቢሽንና ባዛር**

ሀ. በክልሎች የሚዘጋጅ ኢግዚቢሽንና ባዛር መረጃ በማሰባሰብ እና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር በከተማችን የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ ኮታ እንዲያዝላቸው የማድረግ ስራ መሰራት አለበት፡፡

ለ. በክልል ደረጃ ለሚዘጋጅ ኢግዚቢሽንና ባዛር ክልሎች በሚሰጡት ኮታና መስፈርት መሰረት ኢንተርፕራይዞችን በመመልመል የማሳተፍ ስራ መሰራት አለበት፡፡

**10. በውጪ ሀገር ስለሚካሄድ ኢግዚቢሽንና ባዛር**

ሀ. በውጪ ሀገር የሚዘጋጅ ኢግዚቢሽንና ባዛር መረጃ ከፌደራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ባለስልጣን ጋር በጋራ በመስራት በከተማችን የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በኢግዚቢሽንና ባዛር እንዲካፈሉ መረጃ የመስጠት ስራ መሰራት አለበት፡፡

ለ. በውጪ ሀገር ደረጃ በሚዘጋጅ ኢግዚቢሽንና ባዛር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ ከፌደራል አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት ባለስልጣን ጋር ግንኙነት በመፍጠር አጠቃላይ ወጪ እና የተያያዥ መስፈርቶችን መረጃ ለኢንተርፕራይዞች መሰጠት አለበት፡፡

ሐ. በውጭ ሀገር ደረጃ በሚዘጋጅ ኢግዚቢሽንና ባዛር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉ የመመልመል ስራ መሰራት አለበት፡፡

**11. ኢንተርፕራይዞች በኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ እንዳይሳተፉ ስለመከልከል**

**ሀ.** የዕድገት ደረጃ የሌለው ወይም የዕድገት ደረጃውን ያላደሰ ኢንተርፕራይዝ መሳተፍ የለበትም፣

**ለ.** የውጭ ሀገር ምርቶች ይዞ መገኘት የለበትም ፣

ሐ. በንግድ ዘርፍ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከተመረተ ምርት ውጪ ይዞ መገኘት የለበትም፡፡

መ. አምራቾች ከሆኑ በሌሎች ኢንተርፕራይዞች ወይም ድርጅቶች የተመረቱ ምርቶች ይዞ መገኘት የለበትም፣

ሠ. የተሰጣቸውን የኢግዚቢሽንና ባዛር ቦታ በከፊል ወይም በሙሉ ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት የለበትም፣

ረ. በኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ የሚሳተፍ ኢንተርፕራይዝ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ማወክ የለበትም፣

ሰ. ኢግዚቢሽንና ባዛሩን የሚመለከት ማንኛውንም መረጃ ለሚመለከተው አካል መስጠት አለበት፣

ሸ. በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድለት በኢግቢሽንና ባዛሩ ላይ ተሳታፊ ሆኖ መገኘት የለበትም፣

12. **ኢግዚቢሽንና ባዛር ክልከላን በሚተላለፉ ኢንተርፕራይዞች ላይ የሚወሰድ እርምጃ**

ሀ. የተከለከሉ ተግባራትን የተላለፈ ኢንተርፕራይዝ ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት  በኢግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ እንዳይሳተፍ መደረግ አለበት፡፡

ለ. ለሁለተኛ ጊዜ የተከለከሉ ተግባራትን የተላለፈ ኢንተርፕራይዝ በኢግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ለ6 ወር እንዳይሳተፍ መደረግ አለበት፡፡

ሐ. የተከለከሉ ተግባራትን የተላለፈ ኢንተርፕራይዝ ለሶስተኛ ጊዜ በኢግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ለ1 ዓመት እንዳይሳተፍ መደረግ አለበት፡፡

## 19. በኢምፖሪየም ምርትና አገልግሎትን ማስተዋወቅና መሸጥን በተመለከተ.

1. ኢንተርፕራይዞችን በመመልመል ለተወሰነ ጊዜ በኢምፖሪየም ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ እና እንዲሸጡ መደረግ አለበት፡፡

2. ኢንተርፕራይዞች ወደ ኢምፖሪየም ከገቡ በኋላ በኢምፖሪየሙ የአስተዳደር ስርዓት መሰረት የሚተዳደሩ መሆን አለበት፡፡

3. በአምራች ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ከራሳቸው ምርት ውጪ በሌሎች ኢንተርፕራይዞች ወይም ድርጅቶች የተመረቱ ምርቶች ይዘው መግባት የለባቸውም፡፡

## 20. በድረ- ገጽ የሚደረግ የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ

1. የጥቃቅንና አነስተኛ ምርትና አገልግሎቶችን በዘርፍ፣ በምስል፣ በዋጋና በሚገኙበት አድራሻ በዝርዝር በመለየት በቢሮውና በክፍለ ከተማ በሚዘጋጅ ድህረ ገጽ እንዲለቀቅ መደረግ አለበት፡፡

2. ከኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት ለመግዛት ለሚፈልጉ የውጪ፣ የሀገር ውስጥ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የተሟላ መረጃ በድረ-ገጽ በኩል እንዲያገኙ የማድረግ ስራ መሰራት አለበት፡፡

3. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በኤሌክትሮኒክስ ግብይት ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ምርትና አገልግሎታቸውን የማስተዋወቅ እና የመሸጥ ስራ እንዲያከናውኑ ድጋፍ መደረግ አለበት፡፡

## 21. በዳይሬክተሪ የሚደረግ የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ

1. ዳይሬክተሪ በማዘጋጀት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፡፡

2. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት አጠቃላይ መረጃ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማሰባሰብ፣ የማሳተም እና በድረ-ገጽ በመልቀቅ የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፡፡

## 22. በካታሎግ የሚደረግ የማስተዋወቅ ሥራን በተመለከተ

1. ካታሎግ በማዘጋጀት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፡፡

2. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት አጠቃላይ መረጃ በምስል በተደገፈ መልኩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማሰባሰብ፣ የማሳተም እና በድረ-ገጽ በመልቀቅ የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

## የጥሬ ዕቃ አቅርቦት ማመቻቸት

### 24. ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የጥሬ ዕቃ አቅርቦትን ስለማመቻቸት

1. በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በአካባቢ ፣ በክልል እና በውጪ ገበያ በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ያሉባቸውን ችግር በመለየት እና ድጋፍ በማድረግ ተወዳዳሪነታቸውን የማሳደግ ስራ መሰራት አለበት፡፡

2. የኢንተርፕራይዞችን የጥሬ ዕቃ ፍላጎት ለማመቻቸት እንዲቻል በየክላስተር ማዕከሉ የሚገኙ አምራቾች የጥሬ ዕቃ ፍላጎት በዝርዝር በዓይነት፣ በዋጋ፣ በጥሬ ዕቃው መገኛ ቦታ እና በመጓጓዣ ወጪ ተለይቶ መዘጋጀት አለበት፡፡

3. በኢንተርፕራይዞቹ የጥሬ ዕቃ ፍላጎት መሰረት ጥሬ ዕቃ ሊያቀርቡ ከሚችሉ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የጋራ ግዢ ለመፈፀም ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር መደረግ አለበት፡፡

4. በክላስተር ማዕከላት የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የጥሬ ዕቃ ፍላጎታቸውን መሰረት በማድረግ የጋራ ግዢ እንዲፈጽሙ ድጋፍ መደረግ አለበት፡፡

5. በጥሬ ዕቃ አቅራቢነት ለተደራጁ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በክላስተር ማዕከላት ጥሬ ዕቃ እንዲያቀርቡ የማመቻቸት ስራ መሰራት አለበት፡፡

6. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እርስ በርስ፣ በከተማችን ከሚገኙ ተቋማት እና በክልሎች ከሚገኙ ተቋማት ጋር የምርትና የግብዓት ቅብብሎሽ ማመቻቸት ስራ መሰራት አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት

## በየደረጃው የሚከናወኑ ስልጣንና ተግባር

### 25. የቢሮው ስልጣንና ተግባር

1. የገበያ ትስስርን በተመለከተ መመሪያዎችን ያወጣል ያሻሽላል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡
2. የገበያ ልማትና ግብይትን በተመለከተ ለዘርፉ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካለትና ለኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡
3. የሀገር ውስጥ ገበያ ጥናት በማድረግ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የምርት ግብዓትነት የሚያገለግሉ እና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በማጥናት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመረቱበትን ሁኔታዎች የማመቻቸት ስራ ይሰራል፡፡
4. ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ሊያደርጉ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ምርቶቻቸውን በውጪ ሀገር ካሉ ኩባንያዎች ጋር እንዲተሳሰሩ ያደርጋል፡፡
5. በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተደራጁ ኢንተርፕራይዞችን በኤክስፖርት ንግዱ እንዲገቡ ከሚያግዙ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡
6. የክልል የገበያ ዕድሎችን በማጥናት በክልሉ ካሉ የስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ወይም ኤጀንሲ ጋር በመነጋገር አምራችና አከፋፋይ ዮኒዮኖች፤ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ከተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ጋር ትስስር የሚፈጥሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ይሰራል፡፡
7. በአካባቢ የሚገኙ የገበያ ዕድሎችን በጥናት በመለየት ለክፍለ ከተማ እና ለወረዳ ስራ ዕድል ፈጠራ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤቶች መረጃ ይሰጣል፤
8. ወደ ኢምፖሪየም የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በመስፈርቱ መሰረት እንዲመለመሉ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡
9. ለጥቃቅና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአውትሶርሲንግ፣ በፍራንቻይዚግ፣ በሰብ ኮንትራክቲንግ፣ በአውትግሮወር እና በኮንሳይመንት የገበያ ዕድሎችን የማመቻቸት ስራ ይሰራል፣ ያስተባብራል፡፡
10. ጥሬ ዕቃ የሚያስፈልጋቸውን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመለየት ከአምራችና ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፣ስራውን በበላይነት ያስተባብራል፡፡

11. ከተማ አቀፍ ኢግዝቢሽንና ባዛር በማዘጋጀት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞችን ምርትና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃል፡፡
12. በውጭ ሀገር ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ የሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞችን ይመለምላል፣ አስፈላጊውን በጀት ይይዛል፤ ያስተባብራል፡፡
13. ድረ ገጽ፣ ካታሎግ፣ ዳይሬክተሪ፣ መጽሄት፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን፣ ታዋቂ ሰዎችን እና ሌሎች የማስተዋወቂያ መንገዶችን በመመጠቀም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት ያስተዋውቃል፡፡
14. ለጥቃንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተለያዩ ተቋማት የተፈጠረላቸውን የገበያ ትስስር መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል፣ መረጃውንም ለክፍለ ከተማና ለወረዳ በተዋረድ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
15. የተሰጣቸውን የገበያ ትስስር ድጋፍ በአግባቡ በማይጠቀሙ ኢንተርፕራዞች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡ እንዲወሰድም ያስተባብራል፡፡
16. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ግዢ መመሪያ መሰረት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የተደራጁበትን የግል ማህደር እና የታደሰ የዕድገት ደረጃ በኃላፊው ተረጋግጦ የዋስትና ደብዳቤ የብር መጠን ሳይገለጽ እንዲፃፍላቸው ያስተባብራል፡፡
17. ከመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች እና ከከፍተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር እንዲያገኙ ያስተባብራል፡፡
18. በከተማ ደረጃ የተገኘ የገበያ ትስስርን ለክፍለ ከተማዎች በመስፈርት መሰረት የገበያ ትስርርን አከፋፍሎ ይሰጣል ያስተባብራል፡፡
19. ከሸማች ማህበራት፣ ዩኒየኖች፣ የንግድ ምክር ቤቶች እና ከተለያዩ ማህበራት ጋር በቅንጅት በመስራት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ይፈጥራል፡፡
20. በገበያ ልማትና ግብይት ዙሪያ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ሀገራትና ክልሎች በመለየት ተሞክሮ በመውሰድ የተገኙትን ተሞክሮዎች ቀምሮ የማስፋት ስራ ይሰራል ያስተባብራል፡፡

21. በገበያ ልማትና ግብይት ዙሪያ የተሻለ አፈፃፀ ያላቸውን ወረዳዎችና ክፍለ ከተሞች በመለየት ተሞክሮቻቸውን ቀምሮ ለሌሎች ወረዳዎችና ክፍለ ከተሞች የማስፋት ስራ ይሰራል፡፡
22. በገበያ ልማትና ግብይት ዙሪያ መረጃዎችን እና ሪፖርቶችን አጠናቅሮ ይይዛል፣ ለበላይና ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፡፡

## 26. የክፍለ ከተማ የጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር

1. የገበያ ልማትና ግብይት መመሪያዎችን ያስፈጽማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል እንዲሻሻሉ ግብዓት ይሰጣል ፣ያስተባብራል፡፡

2. የገበያ ልማትና ግብይትን በተመለከተ ለዘርፉ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላትና ለኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ ይፈጥራል ያስተባብራል፡፡

3. የሀገር ውስጥ የገበያ ጥናት በማድረግ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊመረቱ የሚችሉ እና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በማጥናት ሁኔታዎች በማመቻቸት መረጃ አደራጅቶ ይልካል፡፡

4. ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ሊያደርጉ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞችን ይለያል፣ መረጃቸውን አጠናቅሮ ያስተላልፋል፣የሚገጥማቸውን ችግሮች በመለየት የተሻለ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፡፡

5. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በኤክስፖርት ንግዱ እንዲገቡ ከሚያግዙ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

6. በአካባቢ የሚገኙ የገበያ ዕድሎችን በጥናት በመለየት ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይሰራል ፣ያስተባብራል፡፡

7. በአካባቢ የሚገኙ የገበያ እድሎችን በጥናት በመለየት ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፣ ያስተባብራል፡፡

8. .ለጥቃቅና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በአውትሶርሲንግ፣ በፍራንቻይዚግ፣ በሰብ ኮንትራክቲንግ፣ በአውትግሮወር እና በኮንሳይመንት የገበያ ዕድሎችን የማመቻቸት ስራ ይሰራል፣ ያስተባብራል፡፡

9. . ወደ ኢምፖሪየም የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በመስፈርቱ መሰረት እንዲመለመሉ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

10. . ጥሬ ዕቃ የሚያስፈልጋቸውን የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመለየት ከአምራችና ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይሰራል ፣ስራውን ያስተባብራል፡፡

11. በጀት በማስያዝ በክፍለ ከተማ ደረጃ ኤግዝቢሽን ባዛር በማዘጋጀት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞችን ምርትና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃል፣ ያስተባብራል፡፡

12.. ድረ-ገጽ፣ ካታሎግ፣ ዳይሬክተሪ፣ መጽሄት እና ሌሎች የማስተዋወቂያ መንገዶችን በመመጠቀም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎት ያስተዋውቃል ያስተባብራል፡፡

13.. ለጥቃንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተለያዩ ተቋማት የተፈጠረላቸውን የገበያ ትስስር መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል፣ መረጃውን በተዋረድ እንዲደርስ ያደርጋል ያስተባብራል፡፡

14. የተሰጣቸውን የገበያ ትስስር ድጋፍ በአግባቡ በማይጠቀሙ ኢንተርፕራይዞች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል ያስተባብራል፡፡

15. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ግዢ መመሪያ መሰረት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የተደራጁበትን የግል ማህደር እና የታደሰ የዕድገት ደረጃ በኃላፊው ተረጋግጦ የዋስትና ደብዳቤ የብር መጠን ሳይገለጽ እንዲፃፍላቸው ያስተባብራል፡፡

16. በክፍለ ከተማው የሚገኙ ከፍተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ግንኙነት በመፍጠር ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

16.ሸማች ማህበራትና ዩኒየኖች የንግድ ምክር ቤቶች እና ከተለያዩ ማህበራት ጋር በቅንጅት በመስራት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገበያ ትስስር ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፡፡

## 27. የወረዳ ስራ ዕድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ስልጣንና ተግባር

1. በገበያ ልማትና ግብይት አሰራር መሰረት የተሰጡትን ተግባራትን ይፈጽማል፡፡

2. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በአካባቢው ከሚገኙ መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በተለያየ አግባብ የሚተሳሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ሁለቱንም አካላት የሚፈልጉትን መለየት፤የማወያየትና ትስስር የሚፈጠርበትን ስልት ይቀይሳል፡፡ ያስተባብራል፡፡

3. በአካባቢው የሚገኙ የመንግስት፤ የግልና ሌሎች ድርጅቶች ለጥቃቅንና አነስተኛ በንዑስ ተቋራጭነት፤በፍራንቻይዚግ፣ በአውትሶርሲንግ እና በኮንሳይመንት የትስስር ሥርዓቶች ተሳስረው የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል ያስተባብራል፡፡

4. በአካባቢው የሚገኙ ኢንተርፕራይዞችን ምርትና አገልግሎቶች ፕሮፋይል በማዘጋጀት ሥራ ሊሰጡ ወይም ምርትና አገልግሎት ሊወስዱ ለሚችሉ ድርጅቶች በልዩ ልዩ ዘዴ ያስተዋውቃል፡፡ ያስተባብራል፡፡

5. በኢንዱስትሪ ማዕከላት በመገኘት ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጋቸውን የጥሬ ዕቃ አይነት በመጠን በዋጋና በጥራት ደረጃ በዝርዝር በመለየት ጥሬ ዕቃው የሚገኝበትንና በጅምላ ግዢ እንዲፈጽሙ ምክርና ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ያስተባብራል፡፡

6. በወረዳ ደረጃ በሚዘጋጁ ኤግዚቪሽንና ባዛሮች በእቅዱ መሰርት በጀት በመያዝ ወቅቱን ጠብቆ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

7. በወረዳ ደረጃ ራሱን ችሎ ኢግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀት ካልቻለ ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፡፡ ያስተባብራል፡፡

8. ወደ ኢምፖሪየም የሚገቡ ኢንተርፕራይዞችን በመስፈርቱ መሰረት ይመለምላል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

9. በገበያ ልማትና ግብይት ሂደት የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉና ሞዴል የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ተሞክሮ እንዲሰፋ ያደርጋል፡፡ ያስተባብራል፡፡

10. የገበያ ትስስር የተደረገለት ኢንተርፕራይዝ ሙሉ መረጃ በተደራጀመንገድ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

11. ከተለያዩ ተቋማት ጋር በሚደረገው የገበያ ትስስር በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንርፕራይዞች የሚሰሩ ስራዎችን በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ያደርጋል

12. ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ሊያደርጉ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞችን የመለየት ስራ በመስራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡

13. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ግዢ መመሪያ መሰረት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የተደራጁበትን የግል ማህደር እና የታደሰ የዕድገት ደረጃ በኃላፊው ተረጋግጦ የዋስትና ደብዳቤ የብር መጠን ሳይገለጽ እንዲፃፍላቸው ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሰባት
## መብቶችና ግዴታዎች

### 28. የገበያ ድጋፍ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች መብት

1. ወቅታዊ የገበያ መረጃ ማግኘት፤
2. የንግድ ስራ አመራር ስልጠና ድጋፍ ማግኘት፤
3. አገልግሎቱን በአካባቢ ገበያ ለማስተዋወቅ በየደረጃው በሚዘጋጁ ኤግዚብሽንና ባዛር ላይ የመሳተፍ እንዲሁም በሌሎች የማስተዋወቂያ ዘዴዎች ምርትና አገልግሎትን ማስተዋወቅ፤
4. ፍትሃዊ የገበያ ትስስር ድጋፍ ማግኘት፤
5. ገበያን በሚያመጡ መንግስታዊ ዝግጅቶች ስልጠና፣ ስብሰባ፣ ልዩ ልዩ ድጋፎች በሚመለከታቸው ላይ መሳተፍ፤
6. በገበያ ትስስር ሂደት በሚፈጠሩ ችግሮች ምክንያት ቅሬታ እና አቤቱታ ማቅረብና መልስ ማግኘት፤

## 29. የገበያ ድጋፍ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዝ ግዴታ፡-

1. መንግስት በሚያደርገው ድጋፍ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስፈልጉ ወቅታዊና ህጋዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ፤
2. በተፈጠረው ገበያ ደረጃውን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት ማቅረብ፤
3. የተገኘውን የገበያ ዕድል መረጃ ለአደራጅ አካል ማሳወቅ፤
4. በጨረታው ሂደት ሲሳተፉ የጨረታውን ሂደት ለማደናቀፍ በማስብ የተጋነነ ወይም ከገበያ በታች የሆነ ዋጋ ያለማቅረብ አለበት፤

## 30. በየደረጃው ያለ የፈጻሚ አካላት መብት

1. ከተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ከስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃ ማግኘት፡
2. ድጋፍ ለማግኘት የቀረቡ መረጃዎች ወቅታዊና ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ፡
3. ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች መንግስታዊና አስተዳዳራዊ ግዴታዎችን እንዲወጡ መከታተል፤
4. የገበያ ዕድል ከሚፈጥሩ ተቋማት አጠቃላይ መረጃ ማግኘት፡

## 31. በየደረጃው ያለ የፈጻሚ አካላት ግዴታ

1. አግባብነት የሌለውና በአሰራር ወይም በዚህ አሰራር ያልተካተተ ድጋፍ ማድረግ የለበትም፤
2. የገበያ ልማት እና ግብይት ስርዓት መመሪያ በአግባቡ የማወቅ፣የማሳወቅ፣የመፈጸም የማስፈጸም ግዴታ አለበት፤
3. የገበያ ድጋፍ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞችን የመደገፍ ፤የመከታተልና የማብቃት፤
4. ፍትሃዊ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት የመስጠት፤
5. ብልሹ አሰራር መታገል፣ መጠቆም፣ በአጥፊዎች ላይ መመስከር እና እርምጃ እንዲወሰድ የማድረግ፤
6. የገበያ ድጋፍ የተደረገላቸውን ኢንተርፕራይዞችን መረጃ በተደራጀ አኳኋን መያዝ፤
7. የገበያ መረጃን ለሁሉም ኢንተርፕራይዞች እኩል እንዲደርስ የማድረግ፤
8. የገበያ እድል ለሚፈጥሩ ተቋማት የሁሉንም ኢንተርፕራይዞች ፕሮፋይል የመላክ፤
9. የገበያ ትስስር ፈጥረው ወይም ለመፍጠር ፈልገው ስለ ኢንተርፕራይዙ ሕጋዊነት ማረጋገጫ ለሚጠይቁ ተቋማት ስለ ተጠየቀው ኢንተርፕራይዝመረጃ አጣርቶ የመስጠት፤

# ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 32. የተጠያቂነት ስርዓት

1. በዚህ መመሪያ የተቀመጡ አሰራሮችን በአግባቡ ያልተገበረ አመራር ወይም ፈፃሚ  አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ መመሪያ የተቀመጡ አሰራሮችን በአግባቡ ያልተገበረ ኢንተርፕራይዝ ከገበያ ትስስር የድጋፍ ማዕቀፍ ውጪ ሆኖ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡

### 33. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮች

ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ማንኛውም መመሪያዎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዬች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

### 34. የተሻሩ መመሪያ

ከዚህ ቀደም ወጥው የነበሩ የገበያ ልማትና የግብይት ሥርዓት መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

### 35. መመሪያውን ስለማሻሻል

ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 36. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ሚያዚያ/2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## ግንቦት/ 2011 ዓ.ም

## አዲስ አበባ